# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፦ ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ግንቦት 20 ቀን 2003 ዓ.ም**

**በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በርሀብ እያለቁ የወያኔ ባለስልጣናት በውስኪና በጮማ በዓላቸውን እያከበሩ መሆኑ ተጋለጠ፤**

**መለስ ዜናዊ ባለሀብቶችን አድኑን ሲል ተማጸነ፤**

**የአዳማ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በፌዴራል ፖሊስ ተደበደቡ፤**

እብሪትና ትዕቢት የወጠራቸው የወያኔ ባለስልጣናት ህዝቡ በርሀብ እንደ ቅጠል እየረገፈ በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ባለበት በአሁኑ ሰዓት የግንቦት 20ን በዓል ምክንያት በማድረግ ከፍ ያለ ድግስ ማድረጋቸው ታወቀ::

የወያኔ ቡድን ከበረሀ መጥቶ የአራት ኪሎ ቤተ መንግስትን የተቆጣጠረበትን 20ኛ ዓመት ለማክበር ከወራት በፊት ውስጥ ውስጡን ኮሚቲ በሚል አዋቅሮ የነበረ ከመሆኑም በላይ ከአዲስ አበባ ጀምሮ እስከ ወረዳ ከተሞች የራሳቸውን ካድሬዎችና ደጋፊዎች ብቻ በመሰብሰብ የተንጣለለ ድግስ አድርገዋል::

ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣበት ከወርሀ ግንቦት 1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ በሀገር እና በህዝብ ሀብት ሲጫወትና ሲቀልድ ከመኖሩም በላይ የሰው ልጆች እንደ ሳር እየታጨዱ የተጣሉበት ዘመን መሆኑን ያስታወሱት መላው የሀገሪቱ ነዋሪዎች ዘንድሮም ዜጎቻችን በርሀብና በችግር በየጉድባውና በየስርቻው እየሞቱ እያዩ እንዳላዩ ......ሰምተው እንዳልሰሙ....... አውቀው እንዳላወቁ...... በመምሰል 20ኛ ዓመት የስልጣን ዘመናቸውን በደመቀ ሁኔታ ለማክበር ከሀገሪቱ ካዝና ከፍተኛ ብር ወጪ መመደባቸው ተጋልጦዋል::

የመለስ ዜናዊን ምስል በውድ ዋጋ በማሰራት በቢል ቦርድ በየአደባባዩ መለጠፍ የጀመረው ይሄው 20 የግፍና የመከራ ዘመናትን ያስቆጠረው አገዛዛቸው አመልካች በዓል ዘንድሮ በደመቀ ሁኔታ

ለማክበር በሚል ከህዝብ ላይ ገንዘብ በመውሰድ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ አድርገው ከጥቃቅን ከተሞች እስከ መዲናዋ አዲስ አበባ ድረስ ከፍተኛ ገንዘብ የወጣባቸው ዝግጅቶች እየተደረጉ መሆናቸው ታውቆዋል::

ባለፉት 20 ዓመታት ከልማት ይልቅ ጥፋት...... ከጥጋብ ይልቅ ርሀብ...... ከእድገት ይልቅ ውድቀት...... በሀገሪቱ አንገሰው ህዝቡን ለችግርና ለርሀብ ሀገሪቱዋን ለድህነት ዳርገው የተቀመጡት እነዚሁ የወያኔ ባለስልጣናት ዘንድሮም ህዝቡ በኑሮ ውድነት አረንቋዋ ውስጥ ተዘፍቆ ባለበትና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎቻችን በርሀብ እየሞቱ ባለበት ወቅት ድል ያለ ድገስ አድርገው በህዝቡ ሞትና መቸገር ሲጨፍሩ መሰንበታቸው የወያኔ ባለስልጣናት እና ጀሌዎቻቸው ማንነታቸውን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው ተብሎዋል::

ጥላቻን እና ድህነትን በሀገሪቱ ህዝቦች ውስጥ ዘርተው ከመከባበር ይልቅ መናናቅ...... ከመቻቻል ይልቅ እርስ በርስ መታገልን ያሰረፀው ወያኔ ዛሬ በህዝቡ ስቃይና ሞት ደስተኛ በመሆን ለራሱ ጥቂት ካድሬዎች እና ደጋፊዎች ድል ያለ ድግስ መደገሱ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ያለውን ንቀት ያሳየ መሆኑም ተጠቁሞዋል::

ወያኔ ለይምሰል አዳዲስ ህጎችን ያወጣ ቢሆንም አንዱንም ተግባራዊ ያላደረገ ከመሆኑም በላይ ሀገሪቱን እና ህዝቦችዋን በማይላውሱበት መልኩ የስንግ ይዞ ድፍን 20 ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን ዘንድሮ ደግሞ ከመቼውም ግዜ በላይ ህዝቡን በርሀብና በኑሮ ውድነት እንዲያልቁ እያደረገ ያለበት ቢሆንም ምንም እንዳልተፈጠረ በማስመሰል ድል ያለ ድግስ እየደገሰ በውስኪና በጮማ ማሳለፉ የሚያሳዝን ነው ተብሎዋል::

ወያኔ ስልጣን ላይ ከተቆናጠጠ ግዜ ጀምሮ የሀገርን ዳር ድንበር እንደ ዳቦ እየቆረሰ በሰሜን ለሱዳን እና ሻዕቢያ በምስራቅ ለጅቡቲና ለመንግስት አልባዋ ሱማሌ በደቡብ ለኬንያ እየሸነሸነ ሲያድል የነበረ ለሀገር እና ለህዝብ ክብር የሌለው ቡድን መሆኑንም ያስመሰከረበት 20 ዓመት ነው ያሉት የሀገሪቱ ህዝቦች በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በኢንቨስትመንት ስም ለባዕዳን ለም መሬቶችን እና ደኖችን እየቸበቸበ ሀገሪቱን ምድረ በዳ እያደረገ የሚገኝ ቡድን ነው ሲሉም ጩኸታቸውን እያሰሙ ይገኛሉ::

አርሶ አደሩን ሚሊየነር አድርጌያለሁ ......ደሀ የከተማ ነዋሪውን አጥግቤያለሁ.....በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁትን ባለ ሀብት አድርጌያለሁ እያለ ያለ አንዳች ሀፍረት እና ይሉኝታ የሚለፍፈው የወያኔ ቡድን 20 የመከራና የስቆቃ ዓመታትን በሚያከብርበት ዕለትም ዜጎች እየሞቱ ቀባሪ አጥተው በየቦታው እየወደቁ ይገኛሉ::

ህዝብ ኑሮውን ለማሸነፍ አቅቶት ከላይ ታች እየባዘነ በሚገኝበት በዚህ ግዜ የወያኔ ቡድን የስልጣን የእድሜ ማራዘሚያ የሆነው የአባይ ግድብ ስራ ተጀመረ በሚል ከህዝቡ ላይ በግዳጅ እየቀማ ከመሆኑም በተጨማሪ ባለስልጣናቱ በዓላችን እጥፍ ድርብ ነው በሚል በውስኪና በጮማ እየተንበሸበሹ ዜጎች በርሀብ እያለቁ መሆኑ የሚያንገበግብ እና የሚያቃጥል ነው ሲልም ህዝቡ በቁጭት እየነደደ ይገኛል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ  የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊና ቡድኑ ግራ በመጋባታቸው የተነሳ የሚይዙትንና የሚያደርጉትን እየተቸገሩ መሆኑ ተጠቆመ:: ከነጋዴው ላይ የንግድ ፍቃዳቸውን ነጥቆ ለወራት ያህል ከስራ ውጭ አድርጎዋቸው የነበረውን ሰሞኑን በድጋሚ ስራ እንዲጀምሩ መማፀኑ ታወቀ::

ሰሞኑን የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በመሰብሰቢያ አዳራሹ ውስጥ ታዋቂ ባለሀብቶችን እና ከፍተኛ ነጋዴዎችን ሰብስቦ በተማጸነበት ወቅት እኛ ካለ እናንተ ባዶ ነን ስለዚህ እርዱን አግዙን እያለ ሲማጸን መዋሉ ታውቆዋል::

መለስ ዜናዊ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ግዜያት ባለሀብቶችን እና ነጋዴዎችን ሰብስቦ ባነጋገረበት ወቅት እኛ ከምንላችሁ በስተቀር አንዲት ጋት ተንዛችሁ ብትገኙ ከባድ ቅጣት ይጠብቃችሁዋል.....ጣት እቆርጣለሁ......የኔን መመሪያና ትዕዛዝ የሚጥስ ደግሞ የውጭ ኃይሎች ተላላኪ ነው እያለ ሲያስፈራራ እንዳልነበረ ሰሞኑን እንደገና ባለሀብቶችን በቤተመንግስት ሰብስቦ ሲማጸን መደመጡ ቡድኑ ግራ መጋባቱን የሚያሳይ ነው ተብሎዋል::

የወያኔ ባለስልጣናት ብቻ ሳይሆኑ ስርዓቱ በሙስና የነቀዘ መሆኑን ያመነው መለስ ዜናዊ ያለ እናንተ ብቻችንን ቆመን መሄድ ስለማንችል የእናንተ እርዳታና ድጋፍ ያሻናል ሲል  ተማፅኖ ማቅረቡ ባለሀብቶችን እንዳስገረመም ታውቆዋል::

የውጭ ኃይሎች ተላላኪ.....ሀገር ቦጥቡዋጭ......የህዝብን ችግር የማይቀርፉ......በሚሉና በሌሎችም ጸያፍ ስድቦች በየአደባባዩ ሲሳደብና ስማቸውን ሲያጠፋ እንዳልነበር ዛሬ ዙሪያ ገባውን ተወጥሮ መንቀሳቀሻ እና መላወሻ ሲያጣ በተለይ በህዝቡ ለይ የተጫነው የኑሮ ውድነት አስከፊ ሲሆንበት የፈጠረው ዘዴ ነው ሲሉም ነጋዴዎቹ ሲገልፁ ተደምጠዋል::

በስብሰባው ላይ የነበሩት ነጋዴዎች እና ባለሀብቶች  በበኩላቸው እናንተ ሲነገራችሁ የማትሰሙ በመሆናችሁ ልንቀርባችሁ አልቻልንም እኛን የምታዩን እንደ ጠላት ነው ወደፊትም ከናንተ ብዙ ችግሮች እስካልተቀረፉ ልንቀርባችሁና አብረን ልንሰራ አንችልም በማለት ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ መስጠታቸውን ተከትሎ መለስ አንገቱን ደፍቶ አፉን በሁለት እጆቹ ይዞ በትካዜ ሲያደምጣቸው እንደነበረም ከተሰብሳቢዎቹ የተገኘው ጥቆማ ገልፆዋል::

በዕለቱ አንድ ባለሀብት እንደተናገሩት ከሆነ ስራ የማታሰሩ ከመሆናችሁ በላይ ዛሬ ስንቱ ባለ ሀብት ነው ስራውን ትቶ በየቤቱ ተቀምጦ የሚገኘው ይሄንን ታውቃላችሁ ነገ እኛም የእነሱ እጣ ፈንታ እንደሚደርሰን አልጠራጠርም ስለዚህ ይህ በሆነበት ሁኔታ አብረን እንስራ ማለቱ ፌዝ ከመሆን አይዘልም ሲሉ እንባ እየተናነቃቸው ሲገልፁ እንደነበር ከስብሰባው ተሳታፊ ባለሀብቶች አከባቢ የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

እብሪተኛው የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ በበኩሉ የምትሉት ለኔ ግልጽ አይደለም እንዲህ አይነት ተፈጽሞ ከሆነ አዝናለሁ እንዲስተካከል ይደረጋል አሁን ግን ዋናው የስብሰባው አጀንዳ አግዙን አብረን እነስራ ነው በሚል ከረር ያለ ልመና እና ተማፅኖ እንዳቀረበም ታውቆዋል::

ከዚህም በተጨማሪ በቅርቡ የጀመሩትን የህዳሴው ግድብ አስመልክቶ መለስ ዜናዊ ለነጋዴ ባለሀብቶቹ እንደተናገረው ከሆነ ከእናንተ ውጭ ይሄን ግድብ ማንም አይሰራውም እናም ቆርጣችሁ ከተነሳችሁ ለናንተ ምንም ማለት አይደለም እያለ ለማግባባት የሞከረ ቢሆንም በዚህ ዙሪያ አንድም ተሰብሳቢ አስተያየት ሳይሰጥ በዝምታ በማለፉ መለስን ሳያስከፋው እንዳልቀረ የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል::

መለስ ከባለሀብቶቹ ጋር ያደረገውን ውይይት በቀጥታ ሙሉ ለሙሉ በቲሌቪዥን ቢተላለፍ ሽንፈቱ ሊጋለጥበት ስለሚችል ተቆራርጦ እንዲተላለፍ የኮሙኒኬሽን ፅህፈት ቤት ኃላፊው በረከት ስምኦን ባዘዘው መሰረት ለሁለት ቀናት ዘግይቶ እንዲሰራጭ መደረጉ ታውቆዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባደረበት ስጋት እና ጭንቀት ባለሀብቶችን ሰብስቦ ቢያነጋግርም ውስጥ ውስጡን እየተለቀሙ የሚታሰሩና በቁም እስር ላይ የሚገኙ ባለሀብቶች ከቀን ወደ ቀን ቁጥራቸው እየተበራከተ የመጣ መሆኑን ያጋለጠው የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ዛሬ ከ10 የማያንሱ ባለሀብቶች ትግራይ ውስጥ በመቀሌና አዲግራት እስር ቤት የታሰሩ መኖራቸውን አጋልጦዋል::

በሀገሪቱ ውስጥ አሉ የተባሉት ባለሀብቶች በገንዘባቸው እንደልባቸው እንዳይነግዱ ገደብ ተጥሎባቸው የውጭ ባለሀብቶች ግን እንዳሻቸው እየፈነጩ የሚገኙበት ከመሆኑም በላይ የተለያዩ የፖለቲካ ታፔላ እየተለጠፈባቸው ለእስርና ለቁም እስር እየተዳረጉ ያሉበት ወቅት መሆኑንም ምንጮቹ ገልጸዋል::

በተለይ የመለስ ሚስት አዜብ መስፍን የተባለችው ባልቲት ከእያንዳንዱ ባለሀብት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ትፈጥርና ለጥቂት ግዜ ወዳጅ መስላ ከቀረበች በሁዋላ መልሳ ጠላት ሆና እያጠቃች ብዙዎቹን ለእስርና ለኪሳራ እየዳረገቻቸው መሆኑን የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ኬኬ የተባለውን ድርጅት ባለቤት አዘቅት ውስጥ የከተተችው እስዋ መሆኑን ምንጮቹ በምሳሌ ያስረዳሉ::

ዛሬ አሉ ከተባሉት ባለሀብቶች ተርታ ብቻ ሳይሆን በላይ የሆነችው አዜብ መስፍን ከሀገር እና ከህዝብ ሀብት ላይ እየዘገነች ከመስረቁዋም በተጨማሪ በሽርክና እያለች ከታዋቂ ነጋዴዎች ጋር ስራ ትጀምርና መሀል ላይ እነሱን እያባረረች ለብቻዋ በዘመዶችዋ ስም እያግበሰበሰች ያለች መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ የኬኬ ባለቤት ኒሳን ዲዝል ገልባጭ መኪናና ሌሎችንም አስመጪና አከፋፋይ ሆኖ በጋራ ሲሰራ ቢቆይም ዛሬ እሱን አባርራ ለብቻዋ በአንድ ዘመድዋ ስም ተቆጣጥራው እንደምትገኝ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ለሀገር እድገት እና ለወገን የስራ እድል የፈጠሩ ባለሀብቶችን እየተከታተሉ የሚያጠቁት የወያኔ ባለስልጣናት በተለይ ኢትዮጵያዊነት ስሜት በውስጡ ጎልቶ አለበት የተባለውን ሁሉ በሙስና እያሳበቡ ከሀገር ጥሎ እንዲጠፋ ከማድረግ እስከ ማሰር የደረሱበት ወቅት መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በሚወስዱት እርምጃ የተበሳጩ ብዙዎቹ ሀገራቸውን ጥለው ለእረፍት እያሉ እየወጡ መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው አስረድተዋል::

ከቅርብ ግዜ ወዲህ እጅግ ስር ሰድዶ የመጣው ባለሀብቶችን እግር ከግር እየተከታተሉ ማጥቃት መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ የወያኔ ቡድን በሚወስደው ዘረኛ እርምጃ የተነሳ ገንዘባቸውን እያሸሹ ውጭ ሀገር እያስቀመጡ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ሌላው ቢቀር በየሰፈሩና በየመንደሩ ቸርችረው የሚኖሩ ነጋዴዎችን ከገበያ ውጭ ለማድረግ ዘይት እና ስኩዋር ከአከፋፋዮች ወስደው እንዳይሸጡ ለወራት ያህል አግደዋቸው መክረማቸው ወያኔ ለነጋዴው ያለውን ጥላቻ አጉልቶ የሚያሳይ ነው ተብሎዋል፡፡

በማን አለብኝነት እና በእብሪት ነጋዴዎች እንዳያስመጡና እንዳይሸጡ የተከለከለው ስኩዋርና ዘይት ለወራት ያህል እራሴ እሰራለሁ ብሎ ጀምሮት የነበረ ቢሆንም ስራው ውስብስብ ከመሆኑ አንጻር ሊሸከመው ባለመቻሉ ሳይወድ በግዱ እንደገና ወደ እነሱው ሊመልሰው ተገድዶዋል፡፡

በሌላ ዜና በቲፒ ዩኒቨርስቲ ተጀምሮ የነበረው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የትምህርት ማቆም አድማ ወደ ተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ተዛምቶ በተለይ የአዳማ ዩኒቨርስቲ ትምህርት ሰሞኑን አቁሞ እንደነበር ታወቀ፡፡

ለኮታ ማሙያ ብቻ ተብሎ በየቦታው የተከፈቱት ዩኒቨርስቲዎች የተሙዋላ የትምህርት መርጃ የሌላቸው.....የምግብ አቅርቦት ጨርሶ ባዶ የሆኑ.....መምህራን በበቂ ሁኔታ ያልተመደቡባቸው..... ከመሆኑም በላይ ግቢው በተለያዩ ችግሮች የተተበተቡ በመሆናቸው ብዙ ተማሪዎች ትምህርት እያቋዋረጡ እንደሚወጡም ታውቆዋል፡፡

ረቡዕ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም ምሽት ጀምሮ በአዳማ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በተከሰተ የምግብ መመረዝ እጅግ ቁጥራቸው የበዛ ተማሪዎች እራሳቸውን እየሳቱ በመውደቃቸው በተፈጠረ ግርግር ለሁለት ሳምንት ያህል ትምህርት መቁዋረጡ ታውቆዋል፡፡

ደህንነቱ ያልተረጋገጠ ምግብ በምንቸገረኝነት ብቻ ለተማሪዎቹ የግብር ይውጣ በሆነ መልኩ በመስጠቱ በተከሰተ የጤና ቀውስ ቁጥራቸው ከአንድ ሺህ በላይ ተማሪዎች ለህመም ተዳርገው ሲሰቃዩ እንደሰነበቱ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል፡፡

ተማሪዎቹ ምሽት ላይ እራታቸውን በልተው ከወጡ ከአንድ ሰዓት በሁዋላ በተፈጠረ የጤና ቀውስ ተማሪዎቹ እራሳቸውን ስተው በየሜዳው በመውደቃቸው የተደናገጡት ሌሎች ተማሪዎች ተረባርበው ወደ የሀኪም ቤት በመውሰዳቸው ህይወታቸው ሊተርፍ የቻለ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ 10 ተማሪዎች ለከፍተኛ ህክምና ጳውሎስ ሆስፒታል እንደተኙ ታውቆዋል፡፡

ከምግብ አቅርቦት እስከ ህክምና አገልግሎት ...ከትምህርት ጥራት እስከ መምህራን ችሎታ ባዶ የሆነው የአዳማ ዩኒቨርስቲ ድንገት በተከሰተው የተማሪዎች ምግብ መመረዝ ህክምና እርዳታ መስጠት ያልተቻለ ከመሆኑም በላይ ተማሪዎቹን ወደ ውጭ ወስዶ ለማሳከም እንዳይችሉ የፌዴራል ፖሊሶች እንቅፋት ፈጠረው እንደነበርም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

በማግስቱም ችግሩን ለህዝብ እናሳውቃለን ብለው ተማሪዎቹ መፈክር በማንገብ ሰልፍ ለማድረግ ከግቢ ውጭ በመውጣት ላይ እንዳሉ የፌዴራል ፖሊስ እና ኦሮሚያ አየተባለ የሚጠራው ክልል ፈጥኖ ደራሽ በጋራ በመሆን በዱላ እና በመሳሪያ ሰደፍ ተማሪዎቹን እየቀጠቀጡ እንዲመለሱ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ ለአንድ ሳምንት ከግቢ እንዳይወጡ በር ተዘግቶባቸው እንደሰነበቱ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

በድርጊቱ የተደናገጡ ተማሪዎች በየሸጡ እየሾለኩ ወደ ቤተሰቦቻቸው የሄዱ ሲሆን ብዙዎቹ እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ እንዳልተመለሱና ትምህርትም እንዳልተጀመረ የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል፡፡